

# ዜና News



በብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተ መጻህፍት ኤጀንሲ የውጭና የህዝብ ግንኙነት አገልግሎት በየሁለት ወሩ እየታተመ የሚወጣ

Published by External and Public Relations Services of NALE

ቅጽ 1 ቁጥር 22 የካቲት 2002









## በኤጀንሲው በአዲሱ መሰረታዊ አሰራር ሂደት ለውጥ የሙከራ ትግበራ ተጀመረ

በአሁኑ ወቅት በተለያዩ የመንግስት ተቋማት እተካሄደ ያለው መሰረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥ የተጠቃሚዎችን ተለዋዋጭ ፍላጎት ለማርካት፣ዘመኑ ለሚጠይቀው ተወዳዳሪነት ራስን ብቁ አድርጎ ለመገኘት፣የፈጣን ለውጥን እድገት ለመቀበልና ለውጡ የሚያመጣቸውን ጥቅሞች ተጋሪ ለመሆን ወሳኝ እንደሆነ አያጠያይቅም።

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻህፍት ኤጀንሲም እንደተቋም ለውጡን ለማምጣት የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎችን ሲያከናውን ቆይቶ ከየካቲት 1 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ በወሳኝ የስራ ሂደቶች ላይ የሶስት ወር የሙከራ ትግበራውን ጀምሯል።

የሙከራ ትግበራው በኤጀንሲው የሚከናወነውን አገልግሎት አሰጣጥ በተቀላጠፈ መልኩ ለማከናወን፣በተለይ ስራና ሰራተኛን በማገናኘት ሰራተኞች የሚጠበቅባቸውን ሙያዊ አስተዋጽኦ ለማበርከት ምቹ ሁኔታን ከመፍጠሩ በተጨማሪ የስራ ተነሳሽነትን እንደሚያጎለብት ይታመናል።

ይህን የሙከራ ትግበራ እውን ለማድረግ በተደረጉ ጥረቶች ሰራተኞችን በሰራተኞች ምደባና ድልደላ ረቂቅ መመሪያ ላይ ከማወያየት ጀምሮ ሌሎች በርካታ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተከናውነዋል። የሙከራ ትግበራው ችግር የሚታይባቸውን አሰራሮች ለማስተካከል፤በጥናት ያልታዩ ስራዎች ካሉም እነዚህ ስራዎች ጎልተው እንዲወጡ፣ባጠቃላይ በሙከራ ትግበራው ወቅት የታዩ ችግሮች መፍትሄ እንዲያገኙ የሚያስችልና ለቀጣዩ ትግበራ መሰረት የሚጥል ነው።

717 Addis Ababa Ethiopia

011-5-15 08 82

011-5-52 64 11

Web site:- http:/ /www.nale.gov.et

e-mail:-nale@ethionet.et

## በሙከራ ትግበራው አፈጻጸም ላይ መግለጫ ተሰጠ

የካቲተ 18 ቀን 2002 ዓ.ም በተደረገው አጠቃላይ ስብሰባ በአዲሱ መሠረታዊ አሠራር ሂደት ለውጥ የሙከራ ትግበራ አፈጻጸም ላይ መግለጫ ተሰጠ፡፡

መግለጫው የሠራተኞችን ምደባ፣ የጥናቱን አተገባበርና የቡድን ስምምነቱን ቻርተር አስመልክቶ ሠራተኞች በግልጽ አውቀውት ወደስራው እንዲገቡ ከማድረግ አንፃር የተሰጠ ሲሆን፣ ይኸው መግለጫ በሚመለከታቸው የስራ ሂደት ተወካዮችና በየስራ ዘርፉ ተጠሪዎች አማካኝነት ሰፋ ባለ መልኩ ተብራርቶ ቀርቧል፡፡

የቀረበውን ገለፃ ተከትሎ ሠራተኞች ከምደባና ከጥናቱ አተገባበር ጋር በተያየዘ በርካታ ጥያቄዎችና አስተያየቶች አንስተው ዲሞክራሲያዊ በሆነ መልኩ ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡፡

በውይይቱ ለተነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች በተሰጠ ማብራሪያም ምደባው ስራን ማዕከል ባደረገ መልኩ የተከናወነና አተገባበሩም የድልድል መመሪያውን መሠረት አድርጎ የተሰራ መሆኑን በግልጽ ለማስረዳት ተሞክሯል፡፡

እንደ አጠቃላይም ይህ በሙከራ ደረጃ የተጀመረውን አዲስ አሠራር እውን ለማድረግ በተደረጉ ጥረቶች ሠራተኞችን በተገቢው ቦታ ከመመደብ ጀምሮ ቢሮዎችን እስከማደራጀት የደረሱ በርካታ ስራዎች መከናወናቸው ተገልጿል፡፡

አሠራሩም አሁን ባለበት ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ያለቀለት ነው ተብሎ የሚታሰብ ሳይሆን የሙከራ ጊዜ እንደመሆኑ በዚሁ የተሞክሮ ወቅት የቴክኖሎጂ ግብአቱን፣ ክፍት ቦታዎችን በተገቢው የሰው ኃይል የማሟላትና አሠራሩን የመፈተሽ ተግባር በከፍተኛ ሁኔታ ክትትል የሚደረግበትና እንደ አስፈላጊነቱም የማስተካከያ እርምጃ የሚወሰድበት ጊዜ ስለመሆኑ አፅንኦት በመስጠት ስፊ መግለጫ ተሰጥቷል፡፡

በመጨረሻም በጥናቱ ውጤት አተገባበር ዙሪያ እያንዳንዱ ሠራተኛ ተገቢው ግንዛቤ ኖሮት በዚሁ አግባብ ወደስራው መግባትና ለስራውም ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀስ የሚጠበቅበትን ውጤት ማስመዝገብ እንደሚገባ በማሳሰብ ስብሰባው ተጠናቋል፡፡

## የ2002 በጀት ዓመት የመጀመሪያው መንፈቅ የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ግምገማ

በኤጀንሲው ጥር 21 ቀን 2002 ዓ.ም በተደረገ አጠቃላይ የሰራተኞች ስብሰባ የ2002 በጀት ዓመት የመጀመሪያው መንፈቅ የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ግምገማ ተካሄደ፡፡

ግምገማው መሰረት ያደረገው ለኤጀንሲው በአዋጅ የተሰጠ ዓላማን ለማሳካት ለበጀት ዓመቱ በዓበይት ተግባራት የታቀዱትን የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ንዑሳን ፕሮግራሞችን ትግበራ ከማስቀጠል፣በፖሊሲ/አዋጅ የተሰጡ ተግባራትን በስርዓት ለማስፈጸም እንዲቻል የሪሶርስ እና የስራ መሳሪያዎችን አቅርቦት ከማሟላት፣የነባር ህንጻ እድሳትን ስራ አጠናቅቆ ለአገልግሎት ከማብቃት፣የመረጃ ሀብቶችን ክምችት ከማሳደግና ከማደራጀት፣ለተገልጋዮች ቀልጣፋ አገልግሎት ከመስጠትና በአግባቡ ተንከባክቦ ለትውልድ ከማቆየት እንዲሁም የኤጀንሲውን ዓላማ ለተገልጋዮች በስፋት ከማስተዋወቅና የስርአተ ጾታና ኤችአይቪ/ኤድስ ጉዳዮችን ሜይን ስትሪም አድርጎ ከማከናወን አኳያ በመጀመሪያው መንፈቅ ዓመት የተከናወኑ ልዩ ልዩ ተግባራት አፈጻጸምን በጋራ መገምገም ላይ ያተኮረ ነው፡፡

በግምገማው በመንፈቅ ዓመቱ በተቋም ደረጃ ከታቀዱ አጠቃላይ የፖሊሲ አፈጻጸም እና ድጋፍ ሰጪ 131 ተግባራት መካከል 110 ከ80% በላይ መከናወኑ፣ከካፒታል ፕሮጀክት እቅድ አፈጻጸም አኳያ የነባሩ ህንጻ ጥገናና እድሳት ስራ ተጠናቅቆና ርክክብ ተፈጽሞ ለአገልግሎት መብቃቱ፤እንዲሁም በኤጀንሲው መሰረታዊ የአሰራር ለውጥ ጥናት ተጠናቅቆ በሙከራ ትግበራ ላይ መገኘቱ፤እንዲሁም ከቀድሞው አገር ግዛት ሚኒስቴር ወደኤጀንሲያችን እንዲዛወሩ ስምምነት የተደረሰባቸው የታሪካዊ መዛግብት ጉዳይ በአጭር ጊዜ መጠናቀቁ በጠንካራ ጎኑ የሚጠቀሱ መሆናቸው በሪፖርቱ ተጠቅሷል፡፡

ከዚሁ ጋር ለመንፈቅ ዓመቱ የታቀዱ 18 ልዩ ልዩ ተግባራት የአፈጻጸም ደረጃቸው ከሚጠበቀው በታች መሆንና የተወሰኑ ተግባራትም ሙሉ በሙሉ ያለመከናወናቸው በደካማ ጎኑ የሚጠቀሱ መሆናቸው ተገልጿል፡፡ እንዳጠቃላይ በመጀመሪያው መንፈቅ ዓመት በተለያዩ ምክንያቶች ያልተከናወኑ ተግባራት ከተከታዩ ሩብ ዓመት ዕቅድ ጋር በተደራቢ ተይዘው ሊከናወኑ እንደሚገባና ከዕቅድ በታች የተከናወኑ ተግባራትም አፈጻጸማቸው በተሻለ ደረጃ መለወጥ እንደሚኖርበት በሪፖርቱ እንደመፍትሄ የተጠቆመ ሲሆን፣ቀሪ የበጀት ዓመቱን እቅድ አስመልክቶም በተያዘው መርሀ-ግብር መሰረት ሙሉ በሙሉ መተግበር እንዳለበት እንዳቅጣጫ በሪፖርቱ ተመልክቷል፡፡

በመጨረሻም ሪፖርቱን ተከትሎ ሠራተኞች ላነሷቸው በርካታ ጥያቄዎችና አስተያየቶች በሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎችና ከመድረክ ተገቢው ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶ ስብሰባውን በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

## በቤተመጻህፍት ሙያ ስልጠና ተሰጠ 3

በኤጀንሲው ከየካቲት 1-26 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ በበጀት ዓመቱ ለ2ኛ ጊዜ ከክልልና ከአዲስአበባ ከተማ ለተውጣጡ 12 የቤተመጻህፍት ሠራተኞች በቤተመጻህፍት አገልግሎት አሰጣጥ፣በክላስፍኬሽን፣በካታሎጊንግና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የእውቀት ዘርፍ ሙያዊ ስልጠና ተሰጠ፡፡

ስልጠናው በአራት መርሀ ግብሮች ተከፍሎ በኤጀንሲው ባለሙያዎች የተሰጠ ሲሆን፣ መሰረታዊ ዓላማው በዘርፉ የሰልጣኞችን የሙያ ክህሎት በማሳደግና ሙያዊ ብቃታቸውን በማረጋገጥ የቤተመጻህፍትን የሙያ ክብር ማስጠበቅና በየተቋማቱ የተሻለ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት እንዲኖር

ማስቻል ነው፡፡

በስልጠናው ማብቂያ ለሰልጣኞች በተዘጋጀ የምረቃ ስነ-ስርዓት ላይ ሰልጣኞች የስልጠና ቆይታቸውን አስመልክተው ሲገልጹ ስልጠናው በተለይ የሰልጣኞችን ሙያ ከማዳበር፣ተገቢውን ክህሎት ከማስጨበጥና መሰረታዊ እውቀትን ከማስያዝ አንጻር እጅግ የተዋጣለት እንደነበር ጠቁመው ለቀጣይ ስራዎቻቸው እንደግብአት በማገልገል ለተሻለ አሰራርና ለተሻለ አገልግሎት ዝግጁ እንደሚያደርጋቸው ገልጸዋል፤አያይዘውም የስልጠና ፕሮግራሙ ደረጃ በደረጃ ቀጣይነት ቢኖረውና የስልጠና ተሳታፊዎችን እንደየሁኔታው የመከታተልና የመገምገም አካሄድ ቢኖር ስልጠናውን የበለጠ ተወዳጅና ውጤታማ ያደርገዋል ብለዋል፡፡

በመጨረሻም በዚሁ የምረቃ ስነ-ስርዓት ማጠቃለያ ላይ ለተሳታፊዎች የተዘጋጀላቸውን የምስክር ወረቀት በመስጠት ፕሮግራሙን በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡